# ፍልስፍና አልባ የሆነ ፖለቲካ የአንድን ህብረተሰብ አስተሳሰብ ያዘበራርቃል- የመጨረሻ መጨረሻም አገርን ያወድማል!

ከረዥም ጊዜ ጀምሮ በብዙ አፍሪካ አገሮች የሚታየው የአስተዳደር ብልሹነት ፣ የህዝቦች ኑሮ መዘበራረቅና ዓላማ-ቢስ መሆን ፣ እንዲያም ሲል በአንድ አገር ውስጥ የሚኖር ህዝብ በሃይማኖትና በጎሳ አሳቦ ርስ በርሱ እንዲጠላላ ማድረግና ፣ የመጨረሻ መጨረሻም ወደ ርስ በርስ መተላለቅ እንዲያመራ መንገዱን ማዘጋጀት ፣ በተራ አነጋገር ከመልካም አስተዳደር እጦት ፣ ከአምባገነናዊ አስተዳደር መስፈንና ከዲሞክራሲ አለመኖር ጋር ሲያያዝ ይታያል። አንዳንዶች እንዲያውም አልፈው እንደዚህ ዐይነቱን ዓላማ-ቢስ የህብረተሰብ ጉዞ የአፍሪካ መሪዎች ወይም የጥቁር ህዝብ ችግር አድርገው የሚመለከቱ አሉ።

በእርግጥ ለአንድ አገር ስርዓት ባለው መልክ መተዳደርና ፣ ህብረተሰቡም በዕቅድና በዓላማ እንዲመራ ከተፈለገ በዚያ የሰፈነው አገዛዝ ህብረተሰቡን በማደራጀት ረገድ የሚጫወተው ከፍተኛ ሚና አለ። ጥያቄው ግን አንድ ህብረተሰብ ዓላማ ባለው መልክ እንዳይደራጅና ቆንጆ ቆንጆ ስራዎችን እንዳይሰራ የሚያግዱት ነገሮች ምን ምን ነገሮች ናቸው? በስነ-ስርዓት እንዲደራጅስ ከተፈለገ መሪዎችም ሆነ ህብረተሰቡ መከተል የሚገባቸው ኖርሞች ፣ ሞራልና ስነ-ምግባር አሉ ወይ? ምንስ ይመስላሉ ? ወይስ አንድ ህዝብ እየተዋከበና ርስ በርሱ እየተፋጠጠ መኖሩ ተፈጥሮአዊ ግዴታ ነው ወይ ? አንድ ህብረተሰብስ በምን መልክ ነው መታየት ያለበት? በሌላ አነጋገር ፣ ለመብላትና ለመጠጣት ብቻ የሚኖርበት? ወይስ ፖለቲካዊ ፣ ባህላዊ ፣ ስነ-ምግባራዊ ፣ ጥበባዊና ኢኮኖሚዊ ፣ እንዲሁም ሌሎችም ነገሮች ተደራጅተው ህብረተሰቡ እንደሰውነታችን በብዙ ነርቮች ተሳስሮ ፣ ልክ እንደደም ዝውውር ሳያቋርጥ ፣ በተለይም ኢኮኖሚው አንድኛው መስክ ከሌላው ጋር በመያያዝ ውስጠ-ኃይሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና እየተጠናከረ የሚጎዝበት መድረክ ነው ወይ ? የሚሉትን ጥያቄዎች ጠጋ ብሎ መመልከትና መመርመር የሚያስፈልግ ይመስለኛል። በተለይም በአሁኑ ዘመን የግሎባል ካፒታሊዝም አይሎ መውጣትና ፣ የብዙ ህብረተሰቦችን ህይወት ወሳኝ ብቻ ሳይሆን ፣ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲያመሩ ማስገደድና ማዘበራረቅ ፣ ብዙ የአፍሪካ አገሮች ፈራቸውን እየሳቱና በቀላሉ የማይመለሱበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ስንነሳ በፍጹም ልናልፈው የማንችለው ጥያቄ ከፊታችን ተደቅኖ ይገኛል። ይኸውም ብዙ የምዕራብ ካፒታሊስት አገሮች ከሞላ ጎደል ስርዓት ባለው መልክ ተደራጅተው ሲጓዙና ፣ የብዙ ሚሊያርድን ህዝቦች ዕድል ወሳኝ መሆን ሲችሉ ፣ እንደኛ ያለውንስ ህዝብ ስነ-ስርዓት ያለው አደረጃጀት ለምን ተሳነው? ስነ-ስርዓትስ ባለው መልክ ለመደራጀት እንዳንችል የሚጎድሉን ነገሮች ምንድናቸው? ተፈጥሮአዊ ፣ ባህላዊ ፣ ህብረተሰብአዊ ? ወይስ የፖለቲካ ፍልስፍና እጦትና መሪዎች የሚመሩበት አንዳች ፍልስፍና አለመኖር ?

ለአንድ ህብረተሰብ በስነ-ስርዓት መደራጀትን አስመልክቶ ከጥንት የግሪክ ስልጣኔ ጀምሮም ሆነ ከዚያ በፊት ህግና ስርዓት አስፈላጊ መሆናቸውን በብዙ ምርምር የተደረሰበትና በኢምፔሪካል ደረጃም የተረጋገጠ ነው። ይሁንና በተለይም ፍልስፍናን ከፖለቲካ ጋር ማያያዝና ፣ አንድም ህብረተሰብ ሚዛናዊ በሆነ መልክና በስነ-ስርዓት የማደራጀትን አስፈላጊነት በከፍተኛ ደረጃ ውይይት የተካሄደበት ከግሪክ ስልጣኔ ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል። ከዚያ በኋላ የተነሱና ብዙም ምርምር የተካሄደባቸው የፖለቲካ ፍልስፍናዎች ፣ ህብረተሰብን በአንድ ስርዓት ባለው መልክ ማደራጀት ፣ በግሪኩ የተለያዩ ፍልስፍናዎች ላይ ተመርኩዞ ነው ማለት ይቻላል። እዚህ ላይ ሌላው የሚነሳው ጥያቄ ፣ የተለያዩ የግሪክ ፈላስፋዎች አትኩሯቸውን ለምን በፍልስፍና ላይ ፣ በተለይም በፖለቲካ ፍልስፍና ላይ አደረጉ ? የሚለው ከባድ ጥያቄ ነው። እንደሚታወቀው የሰው ልጅ እንደማንኛውም ተንቀሳቃሽ ፍጡር ለህይወቱ ምግብ ፣ ውሀ ፣ መጠለያና መከላከያ ቢያስፈልገውም ፣ ከሌላው ፍጡር ጋር ሲወዳደር የማሰብ ኃይልና ራሱንም በማደራጀት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንደሚሸጋገር የታወቀ ነው። ይሁንና የማሰብ ኃይሉን

እንዳያዳብር ፣ አዳዲስ መሳሪያዎችን በመፍጠር ከዝቅተኛ ህብረተሰብ ወደ ከፍተኛ እንዳይሸጋገር ፣ ከቁም ነገር ስራ ይልቅ በሆነ ባልሆነው ነገር በመያዝ ወይም በጦርነት በመጠመድ ዝብርቅርቅ ኑሮ እንዲኖርና ፣ በዚያው እንዲገፋበት የሚያደርጉትና ፣ ይህ ዐይነቱም ኑሮ እንደ ባህልና እንደ ልማድ የሚወሰድበት ሁኔታ አለ። ይህንን ሁኔታ ጠጋ ብለው የተመራመሩት የግሪክ ፈላስፎች የሰው ልጅ ከእንስሳ የተለየ ከሆነና ፣ ራሱንም ማደራጀትና በሰላም መኖር የሚችል ከሆነ ለምንድን ነው ወደ ጦርነት የሚያመራው? ለምንድን ነው የተዘበራረቀ ኑሮ የሚኖረው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ነበረባቸው።

ሶክራተስና ፕላቶ ብቅ ከማለታቸው በፊት በስድስተኛው ክፍለ-ዘመንና ከዚያ በፊት የግሪክ ህዝብ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ይገኝ ነበር። የርስ በርስ መተላለቅ ፣ መጠን የሌለው ብዝበዛና ድህነት ፣ የተፈጥሮ አደጋዎች መደጋገምና ሌሎችም የግሪክን ህዝቦች ኑሮ ያመሰቃቀሉና ፣ ዕረፍትና ሰላም አንሰጥም ያሉ ሁኔታዎች የህዝቡ ዕጣዎች ነበሩ። እነዚህን የመሳሰሉ የኑሮን ትርጉም ያሳጡ ሁኔታዎች በነ ሆሜርና በሄሲዮድም ሆነ በግሪክ ህዝብ ዕምነት የአምላኮች ድርጊት እንደነበርና ፣ ባስፈለጋቸው ጊዜ ህዝቡን ለመቅጣት ሲሉ የሚልኩት ውርጅብኝ እንደነበርና ፣ ህዝቡም ካለ አምላኮች ፈቃድ በራሱ አነሳሽነት ምንም ሊያደረገው የሚችለው ነገር እንደሌለና ፣ የነሱንም ትዕዛዝ መጠበቅ እንደነበረበት የታመነበት ጉዳይ ነበር። ከሶክራተስና ከፕላቶ በፊት የነበሩ የመጀመሪያዎቹ የተፈጥሮ ፈላስፎች ይህንን አስተሳሰብ ትክክል እንዳልሆነና ፣ በተፈጥሮ ውስጥ ይከሰቱ የነበሩ አደጋዎች ፣ ለምሳሌ እንደ ብልጭታና የመሬት መንቀጥቀጥም ሆነ ሌሎች ነገሮች የአምላኮች ተልዕኮዎች ሳይሆኑ የተፈጥሮ ህግጋት እንደሆኑና ፣ ማንኛውም ነገር ካለምክንያት እንደማይከሰት አመለከቱ። ይህ የመጀመሪያው የተፈጥሮ ፍልስፍናና ፣ በአምስተኛው ክፍለ-ዘመን በታላቁ የግሪክ መሪ በሶሎን ተግባራዊ የሆኑት የመጀመሪያው የፖለቲካ ሪፎርሞች በግሪክ ህዝብ አስተሳሰብ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣሉ። ከፍተኛ የባህል ለውጥ የታየበትና ልዩ ልዩ የፍልስፍና አስተሳሰቦችና የሂሳብ ምርምሮችና ሳይንሳዊ አስተሳሰብም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው በተለይም የግሪክን ምሁር ጭንቅላት መያዝ የጀመረውና ዕውነተኛ ዕድገት መታየት የተጀመረበት። በፒታኩስና በሶሎን የአገዛዝ ዘመን የግሪክ ህዝብ ከጦርነት ተላቆና በአጉል ጀግንነት ላይ የተመሰረተን ዝናን ጥሎ ራሱን በማግኘት ዕውነተኛ የሲቪክ አገዛዝን የተቀዳጀበት ዘመን ነበር። የማቴሪያል ደስተኛነት ብቻ ሳይሆን የመንፈስንንም ነጻነትና ደስተኛነት በመቀዳጀት የመፍጠር ችሎታውን ያዳበረበት ዘመን ነበር። ይሁንና ግን ስልጣኔው እየገፋ ሲሄድና የስልጣን ሽግግር ሲመጣና የኃይል አሰላልፍ ሲቀየር ፣ የፖለቲካው አደረጃጀት እነሶሎን በቀደዱት መልክ ሊጓዝ አልቻለም። በተለይም የስልጣንን ምንነት ከራሳቸው ዝናና ጥቅም አንፃር መተርጎምና ተግባራዊ ማድረግ የጀመሩ ተከታዮቹ የግሪክ መሪዎች የፖለቲካውን አቅጣጫ ወደ ማይሆን መንገድ እንዲያመራ ያደርጋሉ። በዚህ ላይ የኦሊጋርኪዎችን አመለካከት የሚያስተጋቡና ይህም ትክክል ነው ብለው የሚያስተምሩ ፈላስፋዎች ፣ ሶፊስቶች ተብለው የሚጠሩ ፣ የፖለቲካውን መድረክ እየተቆጣጠሩና ብዙ ወጣቶችንም እያሳሳቱ ይመጣሉ። በተለይም የአቴን ግዛት አይሎ መውጣትና ከሌሎች ደሴቶች ጋር ሲወዳደር በስልጣኔ ቀድሞ መሄድ የግሪኩን የመጀመሪያውን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ቀስ በቀስ እየደመሰሰው ይመጣል።

የተለያዩ የግሪክ ግዛቶች ፣ በአንድ በኩል በራሳቸው ውስጥ በሚደረግ ሽኩቻ የተወጠሩ ሲሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የፐርሺያ አገዛዝ አቴንና ሌሎችንም ግዛቶች በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ተደጋጋሚ ጦርነት ይከፍታል። ይሁንና በፐሪክለስ የሚመራው የአቴን ግዛት ሌሎችንም በማስተባበር ከፐርሺያ የተከፈተበትን ጦርነት መክቶ ይመልሳል። አቴን በአሸናፊነት ስትወጣ የጥጋብ ጥጋብ ይሰማታል። ቀደም ብሎ የተደረሰበትን የእኩልነት ስምምነት በማፍረስ በሌሎች የግሪክ ግዛቶች ላይ ወረራ ታደርጋለች። እምቢ ያሏትን ግዛቶች ሁሉ በመውረርና ፣ በተለይም ወንድ ወንዱን በመጨረስ ሴቶችንና ህፃናትን ገባርና ባርያ ታደርጋቸዋለች። ድርጊቱ እጅግ አሰቃቂ ነበር። የግሪክን ህዝብ ትርምስ ውስጥ የከተተ ነበር። ይሁንና ይህ የአቴን ጥጋብና ግፍ በስፓርታ ግዛትና አመራር ሊከሽፍና ሊገታ ችሏል። በዚህ ድርጊቱ ፐሪክለስ አቴን ለሌሎች ግዛቶች በስልጣኔዋ ምሳሌ ትሆናለች ብሎ

እንዳለተመጻደቀ ሁሉ ፣ በተግባር ያሳየው ግን በኃይሉ በመመካት ወረራንና ጭፍጨፋን ነበር ያረጋገጠው።

እነ ሶክራተስና ፐላቶ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአምስተኛው ክፍለ-ዘመንና በአራተኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ላይ ብቅ ሲሉ ይህንን የወንድማማቾችን ርስ በርስ መተላለቅና ፣ ህዝቡን ሰላም ማሳጣትና ኑሮም ትርጉም እንዳይኖረው ማድረግ የተረጎሙት በተሳሳተ አመለካከት ላይ የተገነባ ስልጣን መሆኑን በማመልከትና ፣ በአንድ ግለሰብ ላይ ብቻ የሚሳበብ ሳይሆን ፣ ጠቅላላውን የፖለቲካ አወቃቀርና አገዛዙ የሚመራበትን ፍልስፍና በመመርመር ነበር። በሶክራተስ ዕምነትና አመለካከት ፣ በጊዜው ፐሪክለስ ታላቅ መሪ ቢሆንም በሱ ዘመን አቴን ወደ ኢምፔርያሊስትነት የተለወጠችና ፣ የአገዛዙም ዋና ፍልስፋና ዝናን በማስቀደም ኃይልንና ስግብግብነትን(Power and Greed) መመሪያው አድርጎ የተነሳ አገዛዝ መሆኑን በማመልከት ነበር። በመሆኑም ይላል ሶክራተስ ፣ በፐሪክለስ ዘመን ወጣቱ ሰነፍ ፣ ለፍላፊና አጭበርባሪ የሆነበት ዘመንና ፣ አሳሳች አስተሳሰብ በማበብ በተለይም የወጣቱን ጭንቅላት በመያዝ ወደ ማይሆን አቅጣጫ እንዲያመራ የተደረገበት ዘመን ነበር። ባህላዊ ኖሮሞችና መከባበር የጠፋበት ፣ ሽማግሌ የማይከበርበትና ፣ ህዝቡም አንድ ይዞ የሚጓዘው ዕምነት አልነበረውም። አስተሳሰቡ ሁሉ የተዘበራረቀበት ነበር።

በጊዜው የነበረው ትግል ይህንን አቅጣጫ የሌለውን ጉዞና በስልጣን መባለግ አስመልክቶ በሶክራተስና በፐላቶ በአንድ ወገን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በሶፊስቶች መሀከል የጦፈ ትግል ይካሄድ ነበር ። ሶፊስቶች የእነ ፐሪክለስን ስልጣንና ፍልስፍና ሲደግፉ ፣ የአመለካከታቸው የፍልስፍና መሰረት በጊዜው የነበረውን ሁኔታ መቀበልና ይህም ትክክል መሆንኑ ማስተማር ነበር። ሶፊስቶች በአነሳሳቸው ተራማጅ ቢሆኑም ፣ ፍልስፍናቸው በቀጥታ በሚታይ ነገር ላይ ተመርኩዞ ትንተና መስጠትና በጣፊጠ ግን ደግሞ በተሳሳተ አቀራረብና አነጋገር የሰውን ልብ መሳብ ነበር። ስለዚህም በሶፊስቶች ዕምነት ስልጣን ላይ ያለው የገዢ መደብ የሚያወጣውን ህግ አምኖ መቀበልና ፣ ከዚህ ሌላ አማራጭ ነገር እንደሌለ ሲከራከሩና ለማሳመን ሲጥሩ ፣ እነሶክራተስና ፐላቶ ደግሞ በሶክራተስ በመመሰል ይሉት የነበረው የጠቅላላውን የፖለቲካ አወቃቀር ለመገንዘብ ከነበረው ሁኔታ አልፎ(Trnascedental) መሄድና መመርመር እንደሚያስፈልግ ያመለክቱ ነበር። በሌላ አነጋገር ፣ ሶፊስቶች ኃይልንና ለስልጣን መስገብገብን ትክክል ነው ብለው ሲሰብኩ ፣ እነሶክራተስና ፐላቶ ደግሞ እንደዚህ ዐይነቱ ጉዞ እጅግ አደገኛ እንደሆነና ፣ የመጨረሻ መጨረሻም አንድ ህብረተሰብ ሊወጣው የማይችልበት ማጥ ውስጥ የሚከተው ነው ብለው በጥብቅ ያሳስቡ ነበር። ካሊክለስ የሚባለው ሌላው የሶፊስቶች መሪ ደግሞ የነሶክራተሰን በእርቆ አስተዋይነትና በሚዛናዊነት ላይ የተመረኮዘ የፖለቲካ ፍልስፍና ሞኞች ብቻ ናቸው የሚከተሉት ብሎ በመስበክና በማንቋሸሽ ፣ የፖለቲካ ስልጣን በስምምነት ላይ የሚመሰረት ሳይሆን በአሸናፍና በተሸናፊነት ላይ የተመረኮዘና ፣ የመጨረሻ መጨረሻም ኃይል ያለው ብቻ ነው ሊገዛ የሚችለው በማለት ሽንጡን ገትሮ ይከራከር ነበር። በተጨማሪም በሶፊስቶች ዕምነት አንድ ሁሉንም ሊያሰተባብርና ሁሉም ሰው ለቀበለው የሚችለው ዕውነት ነገር የለም። ሁሉም ሰው አንድን ነገር እንደፈለገው ሊተረጉምና ሊረዳ ይችላል። ፕሮታጎራስ የሚባለው የሶፊቶች ሌላው መሪ ማንም ሰው የራሱ የዕውነት መለኪያ(Man is the Measure of Everything) አለው በማለት አንድ ሁሉንም ሊያሰተባብርና ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባው ዕውነት የለም በማለት የሶፊስቶችን የተሙለጨለጨ አመለካከት ያስተጋባ ነበር። የሶፊስቶችም እጅግ አደገኛ ፍልስፍና ተቀባይነት በማግኘቱ ለግሪክ ስልጣኔ መወደቅ ፣ ለህበረተሰብአዊ እሴቶች መበላሸት ዋናው ምክንያት እንድሆነ በታሪክ ተመዝግቧል። በሌላ አነጋገር አንድ አስተሳሰብ መጥፎም ይሁን ጥሩ በአንድ የህብረተ-ሰብ ክፍል ዘንድ ተቀባይነትን ካገኛና እንደመመሪያ ከተወሰደ ፣ አይ ህብረተሰቡ በስልጣኔው ይገፋበታል ፣ መጥፎው ደግሞ አይሎ ከወጣ ግሪክ እንደደረሳብት ዕጣ የመከስከስ ዕድል ያጋጥመዋል ማለት ነው።

በሶክራተስና በፐላቶ የፍልስፍና ዕምነት ግን ማንም ሰው ዓለማና ተግባር ሲኖረው ፣ በመጀመሪያ ከትክክለኛ ዕውነት ጋር ነው የሚፈጠረው። ይሁናን ግን በዚህች ዓለም ላይ ሲወረወር እንደየህብረተሰቡ ሁኔታ ከተፈጠረበት ዕውነት ጋር እየራቀ ይሄዳል።

በአንድ ወቅት ነገሮች ርስ በራሳቸው እንደተያያዙና የተወሳሰቡ መሆናቸውን ይገነዘብ የነበረው ጭንቅላት ፣ የተያያዙ ነገሮችን እየበጣጠሰ መመልከት ይጀምራል። ነገሮች ሁሉ ብዥ ይሉበታል። ዕውነትንና ውሸትን ለመለየት ፣ እንዲሁም ደግሞ ለአንድ ችግር መነሻ የሆነውን ምክንያት ለመረዳት ችግር ውስጥ ይወድቃል። በሶክራተስም ሆነ በፕላቶ ዕምነት ወደ ጥንቱ ሁኔታ ለመመለስ ማንኛውም ሰው ዕውነትን ለመፍለግ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ አለበት። እየመላለሰ ራሱን መጠየቅ አለበት። በቀላሉ በሚታዩ ነገሮች ላይ መማረክና እነሱን ትክክል ናቸው ብሎ መቀበል የለበትም። በሶክራተስም ሆነ በፕላቶ ዕምነት የሰው ልጅ ሁሉ ጠላት ከመንፈሱ ተነጥሎ የሚታየው አካሉ ነው። ሰዎች ራሳቸውን ለማጎልመስ ሲሉ በሆነው ባልሆነው ነገር ይታለላሉ። እየገፉ ሲሄዱ ስግብግብነትንና አብጦ መገኘትን ፣ ሌላውን ሰው ደግሞ ማንቋሸሽና መናቅን እንደ ዋና የኑሮ ፍልስፍናቸው አድርገው ይመለከታሉ። ይህ ዐይነቱ አመለካከትና ከቆንጆ ስራ እየራቁ መሄድና በራስ ዓለም ውስጥ መኖርና መሽከርከር ለጦርነትና ለአንድ ህብረተሰብ መመሰቃቀል ምክንያት ነው ይላሉ።

በሶክራተስም ሆነ በፕላቶ ዕምነት የሰው ልጅ ሁሉ ችግር የማሰብ ኃይል ችግር ወይም የዕውቀት ችግር ነው። ዕውነተኛ ዕውቀት በሶክራተስም ሆነ በፕላቶ ዕምነት ትምህርት ቤት የምንማረው ወይም ሸምድደን እንደ ዳዊት የምንደግመው አይደለም። በሁለቱ ዕምነትም ሆነ ኋላ ብቅ ላሉት የአውሮፓ ፈላስፋዎችና ተመራማሪዎች ፣ ዕውነተኛ ዕውቀት ማለት ራሳችንን እንድናውቅና ፣ ወደ ውስጥ ራሳችንን ለመመልከት እንድንችል የሚያደርገን ፣ የበለጠ ራሳችንን እንድንጠይቅ የሚያስችለን ፣ የተፈጥሮን ህግጋት ጠለቅ ብለን እንድንረዳ የሚያስችለንና ፣ በጥንቃቄም በተፈጥሮ ውስጥ ያሉትን ነገሮች በማውጣትና ቅርጻቸውን በመለወጥ እንድንጠቀምባቸው የሚያግዘን ፣ ህብረተሰብን በስነ-ስርዓትና መልክ ባለው ሁኔታ እንድናደራጅ የሚረዳን ፣ ከሰውነታችን ፍላጎት ይልቅ የመንፈስን የበላይነት በማረጋገጥ በመንፈስ ኃይል በመመራት ከሌላው ተመሳሳይ ሰው ጋር ተሳስቦ መኖር መቻል ፣ በፍጹም የራስን ጥቅም በማስቀድም ዓላማ አለመመራት...ወዘተ. ናቸው። ለተንኮልና ለምቀኝነት ተገዢ አለመሆንና ወደ ብጥብጥ አለማምራትና ፣ ህብረተሰብአዊ ምስቅልቅልነት እንዲፈጠር ሁኔታዎችን አለማዘጋጀት ፣ የማንኛውም የሰው ልጅ ፍጡር ጥረት አርቆ በማሰብ ኃይል በመመራት ወደ እግዚአብሄር ለመጠጋት መጣር ነው። በፕላቶ ዕምነት ሌላው ለአንድ ህብረተሰብ ምስቅልቅል ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ወይም ለጦርነት ምክንያት የሚሆኑ ከሰብአዊነትና ከወንድማማችነት ይልቅ የብሄረ-ሰብ/ጎሳነት (Ethnic Solidarity) ምልክት የሆኑ ቅስቀሳዎች ቦታ ከተሰጣቸው ነው። በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ለሚከሰት ችግር ዋናው ምክንያት የተለያዩ ብሄረሰቦች በመኖራቸው ወይም አንደኛው ብሄረሰብ በሌላው ላይ ጫና ስለሚያደርግ ሳይሆን ፣ በስልጣን ላይ ያሉ ኃይሎች ራሳቸው በሚፈጥሩት ልዩነትና ስልጣን ላይ ለመቆየትና ህዝቡን አደንቁረው ለዘለዓለም ለመግዛት እንዲችሉ የብሄረሰብን ጥያቄ እንደ ፖለቲካ መሳሪያ አድርገው ሳይንሳዊውንና የስልጣኔውን ፈለግ ያሳስታሉ። ስለዚህም ለአንድ ህብረተሰብ ችግር ዋናው መፍትሄ እያንዳንዱ ግለሰብ ከሌላው የማይበልጥ መሆኑን ሲረዳና ፣ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ ብሄረሰቦች መኖር የታሪካዊ ግዴታ እንጂ እንደክፋት መታየት የሌለባቸው መሆኑን ሲገነዘብ ነው። በተጨማሪም ተፈጥሮ ውስጥ የተለያዩ ነገሮች ፣ ለምሳሌ የተለያዩ አበባዎች ፣ የተለያዩ ዛፎችና የተለያዩ ከብቶች መኖር የተፈጥሮን ውበት እንደሚያመለክቱና ፣ የተፈጥሮም ህግና ግዴታ የሆኑትን ያህል ሁሉ ፣ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥም የተለያዩ ብሄረሰቦች ፣ ጥቁርና ቀይ መልክ ያለው ሰው ፣ ረዥምና አጭር ሰው... ወዘተ. መኖር እንደ ውበት መታየት ያለባቸው ነገሮች ናቸው። ስለዚህም በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ብጥብጦች የተፈጥሮን ውስብስብነትና ውበት ለመረዳት ካለመቻልና ጠለቅ ብሎ ለማየት ካለመፈለግ የተነሳ ወይም በተሳሳተ ዕውቀት በመመራት አንድን ህብረተሰብ ለመግዛት መቻኮል ነው። ለዚሁ ሁሉ መፍትሄው ይላል ፕላቶ ፣ ማንኛውም ግለሰብ አርቆ አሳቢነትን በማስቀደም በመፈቃቀር ላይ የተመሰረተ ህብረተሰብ ለመገንባት መጣር ነው። ማንኛውም ግለሰብ ይህንን የዩኒቨርስ ህግ ሲረዳና ስምምነትንና ስርዓትን(Harmony and Order) በጭንቅላቱ ውስጥ ሲቀርጽ በምድር ላይ ዕውነተኛውን ገነት ይመሰርታል።

ወደድንም ጠላንም ከብዙ ሺህ ዐመታት ጀምሮ በዓለም ላይ የተከሰቱ የርስ በርስ መተላለቆች ፣ በአገሮች መሀከል የተካሄዱ ጦርነቶች ፣ ረሀብና የወረርሽኝ በሽታዎች ፣ በዘመነ-ሳይንስ እሰካዛሬም ድረስ ዘልቆ ብዙ የሶስተኛውን ዓለም አገሮች የሚያምሰውና የአንድ አገር ህዝብ እየተሰደደ እንዲኖር ያሚያደርግና ፣ ጊዜ የመጣላቸው ኃይሎች ድንበር እየጣሱ የሌላውን አገር የሚወሩ ፣ እነ ሶክራተስ ከፈለሰፉት የሰብአዊነት (Rational Humanism) ይልቅ ሳይንሳዊ አርቆ-አሳቢነትን( Scientific Rationalism) በማስቀደምና በበላይነት በመመካት ነው። ለምሳሌ ሜስትሮቪክ „The Barbarian Temperament“ በሚለው እጅግ ግሩም መጽሀፉ የሚያረጋግጠው ፣ በሃያኛውና በሃያአንደኛው ክፍለ ዘመን የምዕራቡ ዓለም በሳይንስና በቴኮኖሎጂ ቢራቀቀም ፣ እንዲሁም ደግሞ የሊበራል ዲሞክራሲን ተግባራዊ አድርጌያለሁ ቢልም ፣ የተወሳሰቡ የጦር መሳሪያዎች ፣ የኬሚካልና የባዮሎጂ መርዞች በመስራት በሚያስፈልገው ጊዜ ጠላቴ ነው በሚለው ላይ እንደሚበትንና ብዙ ሺህ ህዝቦችን መጨረስ እንደሚችል ነው። ይህ ዐይነቱ ዕልቂት በፋሺዝም ዘመን በጉልህ የታየና የተረጋገጠ ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ሁኔታ እንደገና ሊከሰት የሚችልበትም ሁኔታ አለ። በኢራቅ ህዝብ ላይ የደረሰው ግፍ ፣ በየቀኑ በአፍጋኒስታንና በፓኪስታን ህዝብ ላይ የሚካሄደው ዐይን የወጣ ዕልቂት ፣ አሁን ደግሞ አንድን አምባገነን ገዢ አዳክማለሁ ብሎ በዚያው አሳቦ በሊቢያ ህዝብ ላይ የሚወርደው የቦንብ ውርጅብኝ የምዕራቡን ዕውነተኛ ገጽታ ነው የሚያሳየን። በተጨማሪም በእንደዚህ ዐይነቱ ቅጥ ያጣ የቦምብ ውርጅብኝ እነዚህ አገሮች እንደገና በእግራቸው ሊቆሙ ወደማይችሉብት ሁኔታ ወስጥ እየተጣሉ ነው። በጣም ከተዳከሙና ሃምሳና ስድሳ ዐመት የሰሯቸው ስራዎች ፣ የገነቧቸው ከተማዎችና የመሰረቷቸው ህብረተሰቦች ከፈራረሱና ከተመሰቃቀሉ በኋላ እንደገና መልሶ ለመገንባት እጅግ አስቸጋሪ ነው የሚሆንባቸው። ሰለጠንኩ የሚለውን የምዕራቡን ዓለም ተንኮል የማይረዱ የሶስተኛው ዓለም መንግስታትና አንዳንድ ነፃ አውጭ ነኝ የሚሉ ድርጅቶች የማያስፈልግ እሳት እየጫሩ መጨረሻ ላይ ማቆም የማይቻል እሳት እየሆነ በመምጣት ላይ ነው። ታላቁ ሺለር እንደሚለን ፣ የሰው ልጅ ከአርስቲቶለስ ጀምሮ ዲሞክራሲ የሚለውን ፅንሰ-ሃሳብ ሰምቷል ፤ ሆኖም ግን በመሰረቱ ከአረመኔ ባህርዩ አልተላቀቀም። ፍሪድርሽ ሺለር ፣ *„ታሪክ ማለት ምን ማለት ነው ፣ ለምንስ ዓላማ የዓለምን ታሪክ ማጥናት አለብን“* በሚለው እጅግ ግሩም ስራው የሰውን ልጅ እጅግ አስቸጋሪ ጉዞ ከመረመርና የግሪክን ስልጣኔና የአውሮፓን የህብረተሰብ ታሪክ ካጠና በኋላ የደረሰበት ድምዳሜ ፣ የሰው ልጅ ህብረተሰብአዊ ባህርይ እንዲኖረውና ታሪክን እንዲሰራ ከፈለገ የግዴታ ውጣ ውረድን ማሳለፍና ከፍተኛ የጭንቅላት ስራ መስራት እንዳለበት በጥብቅ ያሳስባል። ሺለር ይህንን ችግር ለመወጣት የሰው ልጅ ልቡን ከአእምሮው ጋር ማገናኘት እንዳለበት ያስተምረናል። ሺለር እንደዚህ ዐይነቱ ድምደማ ላይ የደረሰው በአስራሰባተኛው ክፍለ-ዘመን በአውሮፓ ምድር በፕሮቲስታንና በካቶሊክ ሃይማኖት መሪዎች የተለኮሰውንና ለብዙ ሚሊዮን ህዝቦች ዕልቂት ምክንያት የሆነውን ሰላሳ ዐመት የፈጀውን ጦርነት በሰፊው ከመረመረና የመሪዎችን የተሳሳተ ፖለቲካ በጥልቀት ካጠና በኋላ ነው። በአስራአራተኛው ክፍለ-ዘመንም እንደዚሁ በጣሊያን አገር ከፍተኛ መተረማመስ ይታይ ነበር። አሪስቶክራሲው ፣ የፊዩዳሉ መደብ ፣ በዚህ ላይ ደግሞ ሃይማኖት ታክሎብት የኢጣሊያን ህዝብ በተስቦ በሽታ ፣ በችጋርና በድንቁርና እንዲሰቃይ ያደርጉ ነበር። አብዛኛው ህዝብ ያልተማረ ስለነበር የአገዛዙን ምንነትና የሃይማኖትን ጫና ሊገነዘብ የሚችል አልነበረም። ሁሉም የየራሱ የዲያሌክት ቋንቋ ይናገር ስለነበር ፣ እንደ አንድ ህዝብ የሚያገናኘውና ችግሩን ሊወያይበት የሚችለው አንድ በሳይንስ የተጠና ቋንቋ አለነበረውም። ህዝቡም አንዳች ህብረተሰብአዊ ኖርም ሳላልነበርው በወቅቱ የህብርተሰቡን እሴቶች የሚበክሉ ፣ እንደማህበረሰብ እንዳይደራጅና ችግሮችን በጋራ እንዳይፈታ አስተሳሰቡን ቆልፈው የያዙ የማያስፈልጉ የብልግና ስራዎች ተሰፋፍተው ነበር። በተለይም ለአንዳንድ ፣ ፍልስፍናን ከሃይማኖት ጋር አጣጥመው ለሚታገሉ ምሁራን እንደዚህ ዐይነቱ አፀያፊና የተመሰቃቀለ ኑሮ ሊዋጥላቸው አልቻለም። በተለይም ዳንቴ ይህንን ሁኔታ በሰፊው ካጠና በኋላ ህዝቡን ሊያግባባ የሚችል በሳይንስ የተጠና አንድ ቋንቋ ይፈጥራል። ይህ እንዲሰፋፋ ያደርጋል። በመቀጠልም ለታዳጊው ትውልድ እንደደመመሪያ የሚሆን „የአምላኮች ኮሜዲ“ የሚባለውን የሰው ልጅ ከጨለማ ዓለም ወጥቶ ብርሃንን እንዲያይ የሚያደርግ ፣ የሰውን ልጅ የተወናበደ ኑሮ በማሳየትና ፣ መፍትሄውም በራሱ እጅ ላይ እንዳለ ያመለክታል። ይህ ታላቅ የሊትሬቸር ስራ በኋላ

ለተነሱት ደቀ-መዝሙሮች መመሪያ በመሆን ለሬናሳንስ መንገዱን ይቀዳል። ባጭሩ የዳንቴ የአምላኮች ኮሜዲ ትልቁ የሌትሬቸር ስራ የሚያስተምረን ፣ አንድን ህዝብ ከጨለማ ጉዞ ወደ ብርሃን ለማውጣትና የስልጣኔውን ቁልፍ ለማስያስዝ የህብረተሰብን ችግር በጥልቀት መረዳት እንደሚያስፈልግ ነው። አንድ ህዝብ ጭንቅላቱ ዕውነተኛ የዕውቀት ብርሃን እንዲፈናጠቅበትና የራሱን ዕድል ራሱ ወሳኝ መሆኑን እንዲያውቅ ማድረግ ከሌትሬቸሩ መማር ይቻላል።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ እያንዳንዱ ግለሰብ በተለይም አገርን አስተዳድራለሁ የሚል እንዴት አድርጎ ስምምነትንና ስርዓትን በጭንቅላቱ ውስጥ ሊቀርጽ ይችላል? እንዴትስ ቆንጆ አስተሳሰብ ከጭንቅላቱ ጋር በማዋሃድ የራሱን ጥቅም ሳያስቀድምና ካለአድልዎ ፣ እንዲሁም የርዕዮተ-ዓለም ሰለባ ሳይሆን አገር ማስተዳደር ይችላል? እንዴትስ ለስልጣኔና ለቆንጆ ስራዎች ታጥቆ ይነሳል? የሚሉትን ጥያቄዎች በዝርዝር እንመልከት።

በብዙዎቻችን ዕምነት ትምህርት ቤት የተማረና ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ኢኮኖሚክስም ሆነ የፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት አጠናቆ በማስትሬት ወይም በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቀ ሁሉ አንድን አገር ማስተዳደርና ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ባለቤት እንድትሆን በማድረግ ሚዛናዊ ዕድገት በማምጣት በስልጣኔ እንድትታወቅና ህዝቦቿም በደስታና በስምምነት እንዲኖሩ ሊያደርግ የሚችል ይመስለን ይሆናል። ከሶክራተስ እስከ ፕላቶን ድረስ ፣ እንዲሁም በኋላ ከ12ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ብቅ ያሉትን አንዳንድ የተገጸላቸውን ፣ ፍልስፍናንና ሃይማኖትን ለማዋሃድ የታገሉ የታላላቅ ቀሳውስትን የትግል ዘዴ ስንመለከት አነሳሳቸው ስልትን የተከተለ ነበር። በወቅቱ የነበረውን የማሰብ ኃይል ችግር በመረዳት እንዴት ይህንን ችግር አስወግዶ የተረጋጋና ሰላም የሰፈነበት ህብረተ-ሰብ መመስረት ይቻላል የሚለው ነበር የሚያስጨንቃቸው። እንደሚታወቀው በዘመኑ በየአገሩ ገና ብሄረ-መንግስት አልተመሰረተም ነበር። ከአስራአራተኛው ክፍለ-ዘመን መጨረሻ ጀምሮ የግሪኩ ስልጣኔ በአዲስ መልክ ሲስፋፋ መሰረተ-ሃሳቡ በፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ነበር። በአንድ ነገር ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ሁለ-ገብ(Holistic) የሆነና መንፈስን በከፍተኛ ደረጃ በማደስ የመፍጠር ችሎታን ማዳበር ነበር። ስለሆነም ፣ ትግሉ በጥበብ ላይ ፣ በዕደ-ጥበብ ላይ ፣ በአርክቴክቸር ላይና እንዲሁም ለህብረ-ብሄር የሚያመቹ ትላልቅ ህንጻዎችን ፣ ካቴድራሎችንና የገበያ አዳራሾችን በመስራት የህዝቡን አስተሳሰብ በመሰብሰብ ብሄራዊ ባህርይ እንዲኖረው ማድረግ ነበር። ይህም እንደበፊቱ ከፍተኛ የጭንቅላት ስራን የጠየቀና ቀስ በቀስም በአስራሰባተኛው ክፍለ-ዘመን ለተነሳው የሳይንስ እንቅስቃሴ በሩን የከፈተ ነው። የሰዎች አስተሳሰብ ቀድሞ ብለው በተወሰዱት ምሁራዊ እንቅስቃሴዎችና የከተማ ግንባታዎች ባይታደስ ኑሮ ሳይንሳዊ ፈጠራ ወይ አይቻልም ነበር ፣ ካለበለዚያም ደግሞ በጣም ይዘገይ ነበር። በአስራሰባተኛው ክፍለ-ዘመን እንደገና የአውሮፓ ህዝብ እርስ በርሱ ሲከሳከስና በብዙ ቦታዎች ከፍተኛ ችግር ሲከሰት እነ ላይብኒዝ ፣ በኋላ ዳግሞ ሺለርና ሌሎችም የችግሩን ምንጭ የተረዱት የሰውን የማሰብ ኃይል ድክመት በመረዳት ነው። ባጭሩ ከጥንቱ የግሪክ ስልጣኔ ጀምሮ እስከ አስራሰባተኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ በፈላስፋዎች ፣ በገጣሚዎች ፣ በህንፃ ስራ አዋቂዎች ፣ በሰአሊዎችና በሙዚቃ ደራሲዎች የተካሄደውን ሁለ-ገብ ትግል ስንመለከት ፣ ትግላቸው ስልትንና ዓላማን የተከለ ነው። የትግላቸውም ዋና ዘዴ ችግርን መፍጠር ሳይሆን የሰውን አስተሳሰብ በማጽዳት ለቆንጆ ስራ እንዲነሳሳ ማድረግ ነበር። ከተማሪው እንቅስቃሴ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ያለውን የኛን አገር የምሁራን ትግል ስመረምር ግን ትግሉ በሙሉ ችግር ለመፍጠርና ወደ ግብግብ ለማምራት የሚመስል እንጂ በምንም ዐይነት ያለንን ችግር ፊቶ ወደ ተረጋጋ ሁኔታ ሊያሸጋግረን የሚችል አልነበርም ፤ አይደለምም። የአውሮፓን ታላላቅ የፍልስፍና ምሁራንና ሳይንቲስት ጽሁፎች ስንመለከት ግን የቱን ያህል የሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ገብተው መመርመር እንደቻሉና ፣ ካለአእምሮ ምንም ነገር መደረግ እንደማይችል ከጽሁፎቻቸውም ሆነ በተግባር ካሳዩት ብዙ ነገር መማር እንችላለን። ስለሆነም እንደየሁኔታው የማንኛውም ሰው ልጅ አእምሮ/መንፈስ ጥሩም ሆነ መጥፎ ሆኖ ሊገነባ እንደሚችል በሚገባ የተረዱ ነበር። በተበላሸና ገለብ ገለብ ባለ ትምህርት የተበከለ አእምሮ ለተዛባና ለምስቅልቅል ሁኔታ መንገድን እንደሚያመቻች ከታሪክ መገንዘብ እንችላለን። ለዚህም ነው እነ ሶክራተስም ሆነ ከሁለት ሺህ ዐመት በኋላ ደግሞ እነ ሺለር ለአእምሮ/መንፈስ ከፍተኛ ቦታ በመስጠት

ትግል ያደረጉት። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ከህጻንነቱ ጀምሮ ከጥሩ ዕውቀት ጋር ማደግ ካልቻለ ፣ አስተሳሰቡ ቀና ሆኖ ካለተቀረጸ ፣ በተለይም አድልዎ የበዛበት ፣ ከቆንጆ ስራ ይልቅ ቆሻሻና የተዝረከረከ አሰራር እንደባህል ተደርጎ በሚወሰድበት ህበረተሰብ ውስጥ ተወልዶ ያደገ ህጻን ትምህርት ቤት ከገባ በኋላ ደግሞ በጥሩ ዕውቀት ተኮትኩቶ ካላደገ ስራው ሁሉ ተንኮልና ጥፋት ይሆናል። ጥሩ ትምህርት ከፍተኛ ሚና ቢኖረውም ለአንድ ልጅ አስተሳሰብ ዕድገት ቤተሰብና አካባቢም ከፈተኛ ሚናን እንደሚጫወቱ የተረጋገጠ ነው። እንደሚባለው ማንኛውም ሰው የቤተሰቡና የአካባቢው ግልባጭ ነው። መንፈሱ ተረብሾ ያደገ ፣ ከመጀመሪያውኑ በተንኮል  ጭንቅላቱ የተወጠረ ፣ እየሸመደደ በጣም ጥሩ ውጤት ቢያመጣም ይህ ማለት ስልጣኔ ገብቶታል ማለት አይደለም ፤ ለስልጣኔና ለእኩልነት ሽንጡን ገትሮ ይታገላል ማለት አይደለም። የዕውነት ጠበቃ ይሆናል ማለት አይደለም። ስለሆነም አንድ ሰው በዚህ ወይም በዚያኛው ርዕዮተ-ዓለም እመራለሁ ቢልም ፣ ይህ ማለት ግን ቀናና ጥሩ ሰው ፣ እንዲሁም ከተንኮል የጸዳ ነው ማለት አይደለም። አብዛኛውን ጊዜ ርዕዮተ-ዓለም ሽፋን እንጂ የአንድን ሰው ምንነት መግልጫ አይደለም። አንድ ሰው ማርክሲስት ነኝ ወይም ሊበራል ነኝ ፣  ወይም ደግሞ ይህንኛውን ወይም ያኛውን የፖለቲካ ዕምነትና ሃይማኖት እከተላለሁ ስላለ ፣ እነዚህ ተቀጥያዎች ድብቅ ዓላማውን የሚገልጹ ወይም ማንነቱን የሚያሳዩ አይደሉም። ወይም አንድ ሰው ሊበራል ነኝ ስላለ የተቀደሰ ዓላማ ፣ ማርክሲስት ነኝ የሚለው ደግሞ የሰይጣን ዓላማ አላቸው ማለት አይደለም። እነዚህም በራሳቸው ግለሰቦች ፣ በግለሰብ ደረጃም ሆነ በፓርቲ ተደራጅተው ምናልባትም የራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ተግባራዊ ለማድረግ የሚታገሉባቸው መሳሪያዎች እንጂ በራሳቸው ዕውነተኛ ስልጣኔ አጎናጻፊ ርዕዮች አይደሉም። እንዲያውም ዕውነተኛውን የስልጣኔ ፈለግ የሚሸፍኑና ወደ ሌላ ውዝግብ ውስጥ የሚከቱን ናቸው። ዛሬ በንጹህ የካፒታሊዝም ሊበራል ስርዓት ውስጥ እያለን እንኳ ዓለም ወደ ሰላም እያመራች አይደለችም። እንደምናየው የዓለም ህዝብም ብልጽግናን እያየ አይደለም። ጦርነትና ድህነት በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የሀብት ዘረፋንና ሀብትን ማከማቸት የሰው ልጅ እጣ ሆኗል ማለት ይቻላል።

ከዚህ አጭር ትንተና ስንነሳ እስከአስራስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ የነበረውን የህብረተሰብ ፕሮጀክትና ስልጣኔ መረዳት የምንችለውና ፣ በብዙ የአውሮፓና የአፍሪቃ አገሮች የስልጣኔ ልዩነት እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ የምንገነዘበው ፣ የላይኛውን አጠር ያለ ሀተታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባንም እንደሆን ብቻ ነው። ከአስራስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ወዲህ ካፒታሊዝም የበላይነትን እየተቀዳጀ ሲመጣ ደግሞ የስልጣኔው ፕሮጀክት እየተደመሰሰና የዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ፣ በተለይም የአፍሪቃ ሁኔታ እየተበላሸና እየተዘበራረቀ ይመጣል። የካፒታሊዝም ተልዕኮ ስልጣኔ መሆኑ ቀርቶ በጉልበት ላይና በስግብግብነት ፣ እንዲሁም በማጭበርበር ላይ በመመርኮዝ ብዙ የሶስተኛውን ዓለም አገሮች መቀመቅ ውስጥ ይከታቸዋል። ህበረተሰቦች በጤናማ መሰረት ላይ እንዲገነቡ ከማድረግ ይልቅ መንግስታትን በልዩ መሳሪያ በማስታጠቅና በማማከር ወደ መፋለሚያ መድረክ ይቀይራቸዋል። በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት መፈጸሚያ በኋላ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሙሉ በሙሉ በአሸናፊነት ሲወጣ ተልዕኮው ህብርተሰቦችን ማዘበራረቅና በህብረተሰቦች ውስጥ ግጭት እንዲፈጠር ሁኔታውን ማመቻቸት ሆነ ተግባሩ። ለዚህ ደግሞ የትምህርት መስኩ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል። የአንድን ሰው አእምሮ ስትቆጣጠረውና በገንዘብ ስትገዛው የህብረተሰቡንም አቅጣጫ ታዛንፋለህ። የስልጣኔውን መንገድ ሁሉ ታጨልማለህ። አብዛኛው ህዝብ የማሰብ ኃይሉ ሲዳከም በቀላሉ ወደ ባርነት ትለውጠዋለህ። የዓለም ገበያና የዓለም ንግድ ፣ እንዲሁም ለዚህ እንዲያመች ተብሎ የረቀቀው የኢኮኖሚክስ ትምህርት ዋናው ዓላማቸው የብዙ አፍሪካ ህዝቦችን ዕድል በዚህ ዐይነት የካፒታሊስት ሎጂክ ውስጥ እንዲሽከረከሩ በማድረግ ለዝንተዓለም ባርያ አድርጎ ማስቀረት ነው። ለምሳሌ ለትምህርት ቤትና ለዩኒቨርሲቲ ተብሎ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የተዘጋጀውን የኢኮኖሚክስ መማሪያ መጽሀፎች ለተመለከተ ፣ እንደዚህ ዐይነቱ ተቀባይነት ያገኘ(Conventionalism or normative positivism) የመማሪያ መጽሀፍ በራሱ አርቀን እንዳናስብና የዕውነተኛን ስልጣኔን ትርጉም እንዳንረዳ ሊያደርገን በቃ። ዕድገትንና ስልጣኔን ከህብረተሰብ አወቃቀርና ከታሪክ አንፃር ፣ እንዲሁም የተለያዩ አገሮችን ልምድ መሰረት አድርጎ እንደመነሻና እንደመመሪያ ከመወሰድ ይልቅ ፣ ርዕዮተ-ዓለምንና የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍል ጥቅሞችን የሚያንፀባርቅ ትምህርት በመማር የታሪክ ወንጀል ተሰራ ፤

እየተሰራም ነው። የሳይንስና የቴክኖሎጂን ዕድገት ስንመለከት ግን ንፁህ የምርምርና የጭንቅላት ውጤቶች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። ኢኮኖሚክስ ጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ከፊዚክስ ፣ ከኬሚስትሪና ከባዮሎጂ ጋር ሲያያዝ ብቻ ነው። ይህንን መሰረተ-ሃሳብ ያላካተተ ወይም ያላደረገ የኢኮኖሚክስ ትምህርት የመጨረሻ መጨረሻ አገሮችን መቀመቅ ውስጥ ነው የሚከታቸው። ለምሳሌ በኢኮኖሚክስ ታሪክ ውስጥ መርካንትሊዝም ፣ ፊዚዮክራሲ ፣ በእነአዳም ስሚዝና ፔቲ ፣ ኢንዲሁም ሪካርዶ የሚወከለው ክላሲካል ኢኮኖሚክስ ፣ ይህንን እያረመ ወይም እያስተካከለ የወጣው የማርክሲስት ኢኮኖሚክስ ፣ ከዚያ በኋላ ማርክሲዝምን በመቃወም የወጣው የማርጂናሊስት ወይም የኒዎ-ክላሲክል ፣ ዛሬ ደግሞ ኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚክስ ተብሎ የሚታወቀው ፣ በእነ ሹምፔተር የሚወከለው ኢቮሉሺነሪ ኢኮኖሚክስ ፣ በቬብለን ቶርስታይን የሚወከለው የኢንስቲቱሽን ኢኮኖሚክስ ፣ ብዙ የምዕራብ አውሮፓ ኢኮኖሚዎች የተገነቡበት ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ፊዚካል ኢኮኖሚክስ እየተባለ የሚታወቅ በጣም ጠቃሚ ዕውቀት ፣ እነዚህ ሁሉ የኢኮኖሚክስ ዘርፎች ናቸው። ተማሪው ይህንን ሁሉ እንዳያውቅና ፣ በተለይም ምዕራብ አውሮፓ የአደገበትን ምስጢር እንዳይገነዘብ በሃያኛው ክፍል-ዘመን በእነሳሙኤልሰንና በሌሎች የተደረሱት እንደ መማሪያና ሌላ አማራጭ የሌለ ይመስል ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠር የአፍሪካ ምሁራን ሊሳሳትና ለየአገሩ ድህነት እንደ ዋና ምክንያት ሊሆን በቅቷል። የኢኮኖሚክስ ትምህርት በተለይም በተወሳሰበ የማቲማቲክስ ሞዲል በማሸብረቅና ከተጨባጭ ሁኔታዎች በመራቅ ህብረተሰብአዊ ችግሮችን መፍታት እንዳይቻል አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጠረ። ይህ ብሄቨሪያል ኢኮኖሚክስ(Behavorial Economics) እየተባለ የሚታወቀው ዋናው ዓላማው ፣ የሰውን ልጅ የፍጆታ አጠቃቀም በማቲማቲካል ሞዴሎች ማኑፕሌት ማድረግ እንደሚቻል ማውጣትና ማውረድ ሲሆን ፣ በየጊዜው ሊለዋጡ የሚችሉ ነገሮችን በሙሉ ሊያካትት የሚችል ሞዴል አይደለም። የሰው ልጅ አስተሳሰብ በጣም የተወሳሰብና እንደየሰው የዕውቀት ደረጃ አንድ ቦታ ላይ የረጋ ስላልሆነ ብዙ ነገሮችን አስቀርቶና በጥቂት ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ሞዴል ማውጣት እጅግ አሳሳችና በግልጽ የሚታዩ ችግሮችን እንዳይፈቱ የሚያደርግ ነው። ስለሆነም የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች የበላይነትን በመቀዳጀት ከዩኒቨርሲቲ አልፈው ኢንስቲቱሽኖችን ሁሉ በመቆጣጠር አብዛኛው ህዝብ ዐይኑን እንዳይከፍትና የዕውነተኛ ዕድገትንና ስልጣኔን ትርጉም እንዳይረዳ ለማድረግ በቅተዋል። *ለዚህም ነው ሶክራተስ ፣ ፕላቶና የእነሱን ፈለግ ይዘው የተነሱ ምሁራን ሁሉ ተቀባይነት ያገኘን ዕውቀት-መሳይ ነገር አጥብቀው የታገሉት። ምክንያቱም ተቀባይነት ያገኘ ነገር ሁሉ ካለንበት ቦታ ርቀን እንዳንሄድ ያደርገናል። በማሰብ ኃይል ልንፈታ የምንችላቸውን ችግሮች እንዳንፈታ መንገዱን ሁሉ ይዘጋብናልና።*

ከዚህም በመነሳት ጠለቅ ብለን ነገሩን ለመረዳት ወደ አገራችንና ወደ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ችግር ስንመጣና ሁኔታውን ለመረዳት ስንጥር የግዴታ የላይኛውን ትንተና ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለብን። የኛንም ሆነ የሌሎች አፍሪካ አገሮችን የተወሳሰበ ችግር ስንመረምር ፣ ብዙ የአፍሪካ አገሮች አውሮፓውያን እስከ አስራሰባተኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ የጓዙበትን የምሁር ውይይትና ምርምር እንደልምድና ትምህርት አድርገው ሊወስዱ አልቻሉም። ይህ ችግር ከምን የመነጨ ነው? አንደኛ የብዙ አፍሪካ አገሮች ህብረተሰብ አወቃቀር ከብዙ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ጋር ሲነፃፀር ይለያል። ብዙ የአፍሪካ ህብረተሰቦች ከሌላው ዓለም ጋር የነበራቸው በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ግኑኝነት እጅግ የላላ ነበር። ለምሳሌ የግሪክ ስልጣኔ በአረቦችና በአይሁዲዎች አማካይነተ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ላቲን እየተተረጎመ ወደ አውሮፓ ሲገባና ሲስፋፋ ፣ ብዙ አፍሪካ አገሮች ይህ ዕድል አላጋጠማቸውም። ሁለተኛ ፣ የብዙ ምዕራብ አውሮፓ የህብረተሰብ አወቃቀር በሩቅ ንግድ አማካይነት ሲሸረሸርና ውስጠ-ኃይል በማግኘት ወደ ተሻለ የህብረተሰብ አወቃቃር ሲሸጋገር ፣ አብዛኛዎቹ አፍሪካ አገሮች ይህ ዐይነቱ ዕድል አላጋጠማቸውም። ህብረተሰቡም በተለያየ አስተሳሰብና ዕውቀት ያልተከፋፈለና በሃሳብ ዙሪያም ትግል የማድረግ ባህል የዳበረ ባለመሆኑ ህዝቡን በአስተሳሰብ ለማገናኘት የሚቻልበት ሁኔታ ገና አልተፈጠረም ነበር። በአስራአምስተኛው ክፍለ-ዘመን በባሪያ ንግድና በአስራዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን ደግሞ በቅኝ አገዛዝ አማካይነት ህብረተሰብአዊ አወቃቀራቸው ይበላሻል። በማበብ ላይ የነበረው የስራ ክፍፍል ይኮላሻል። አብዛኛዎቹ አፍሪካ አገሮች ለምዕራብ አውሮፓ ጥሬ-ሀብት አቅራቢ ብቻ እንዲሆኑ ይፈረድባቸዋል። ለዚህም የየመንግስታቱ አወቃቀር ወደ ውስጥ

ዕድገትንና ስልጣኔን እንዳያመጣ ሆኖ ይዘጋጃል። ከቅኝ አገዛዝ መላቀቅ በኋላ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዲስ የተፈጠረው የኃይል አሰላለፍ የአፍሪካን ዕድገት የሚጻረር ይሆናል። በአውሮፓው ምድር ፍጻሜ ያገኘው ጦርነት ወደ አፍሪካና ወደ ሌሎች የሶስተኛው ዓለም አገሮች ይሸጋገራል። አውሮፓውያን በሳይንስና በቴክኖሎጂ ሲበለጽጉ አፍሪካ በጦርነት መድማት አለባት ፤ ህዝቦቿም የሰከነና የሰለጠነ ኑሮ መኖር የለባቸውም ፤ መዋከብና መበዝበዝ ዕጣቸው መሆን አለብት። ለዚህ ደግሞ ፍልስፍና አልባ የሆኑ መሪዎች እንደ አሻንጉሊት በየቦታው ተቀመጠዋል። በተዋቀራላቸው የስለላ መሳሪያ ፣ በሰለጠነላቸው ወታደርና የፖሊስ ሰራዊት አማካይነት ማንኛውንም ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ማፈንና ብልጽግና እንዳይመጣ ማድረግ አለባቸው። በአገራችንና በሌሎች አፍሪካ አገሮች የተቋቋሙት የወታደር ተቋሞች ፣ የስለላ መዋቅሮችና የፖሊሲ ሰራዊት በመሰረቱ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተፈጠረውን ኃይል አሰላለፍ የሚያንፀባርቁና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘረጋውን የአገዛዝ ሰንሰለት አጋዦችና ታዛዦች እንጂ ከየህብረተሰቦቻቸው ፍላጎት አንፃር ከታች ወደ ላይ ቀስ በቀስ እየተደራጁና ሲቪክ የሆነ ባህርይ እንዲኖራቸው ሆነው የሰለጠኑ አይደሉም። በዚህም ምክንያት በብዙ የአፍሪካ አገሮች ኢትዮጵያንም ጨምሮ የሲቪልና የወታደሩ ቢሮክራቶች እጅግ አረመኔና ህብረተሰብአቸውን ለውጭ ኃይል አሳልፈው እንዲሰጡ የተዘጋጁ ነው የሚመስሉት።

በዘመነ-ግሎባላይዜሽን ሁኔታው ምስቅልቅልና ለብዙ ምሁራንና የፖለቲካ ተዋናዮች ግልጽ ያልሆነ ሁኔታ የተፈጠረበት ዘመን ነው። ዛሬ በቡዙ የአፍሪካ አገሮች አምባገነንነት ሰፍኗል ፤ ዲሞክራሲ የለም እየተባለ የሚለፈፈውና የሚወደሰው ይህንን ውስብስቡን የዓለም ሁኔታ ለመመርመር ካለመቻል የተነሳ ነው። የብዙ የአፍሪካ አገሮች ችግር ፐላቶ እንደሚለን ዕውነትን ከውሸት ለመለየት የሚያስችል ዕውቀት ለመስፋፋት አለመቻሉና ፣ ዕውነተኛ ሁለ-ገብ የሆነ ምሁራዊ እንቅስቃሴ አለመኖሩ ነው። ሰፋ ያለ የዳበረ ምሁራዊ እንቅስቃሴ በሌለበት አገር የውጭ ኃይሎች ከውስጡ ኃይል ጋር በማበር የጨለማውን ዘመን ያራዝማሉ። የጭቆና መሳሪያዎች እየላኩና እያስታጠቁ የጸጥታ ኃይል በሚሉት አማካይነት አንድ ህብረተሰብ ተዋክቦ እንዲኖር ያደርጋሉ። ህብረተሰቦች ታሪክ የሚሰራባቸው ፣ ህዝብ ተራጋግቶ እንዲኖር ነገሮች በስነስርዓት ከሚዘጋጅባቸው ይልቅ ወደጦርነት አውድማ መቀየር አለባቸው። ዕውነተኛ ህብረተስብአዊ ሀብትን በማይፈጥር በተራ ሽቀጣ ሸቀጥ አማካይነት ህብረተሰብን ማዋከቡ በከፍተኛ ፍጥነት መካሄድ አለበት። እንደ አገራችን ባሉት ደግሞ ከሌሎች ነገሮች ጋር ተደምሮ የኮሞዲቲ ገበያ የሚባል በማቋቋም ሰፊው ገበሬ አመለካከቱን ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲያዞር በማድረግ ለዓለም ገበያ የቡናና የሰሊጥ ምርት አቅራቢ ፣ ለውስጥ ጌቶች ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እንዲሆን ተደርጓል። በዶክተር ኤልኒ ገብረመድህን የተቋቋመውና የሚመራው የኮሞዲቲ ገበያ ዋና ዓላማው ኢትዮጵያ ውስጥ የተስተካከለ ዕድገትና ዕውነተኛ ስልጣኔ እንዳይመጣ ማድረግ ነው። ይህ በግሎባላይዜሽን ዘመን ንቃተ-ህሊናቸው የደከሙ ህብረተሰቦችን እየፈለጉ ፣ በኒዎ-ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም የሰለጠኑ እንደዚህ ዓይነት ተውረግራጊዎችን እየፈለጉና እያሰለጠኑ ፣ በአንድ በኩል ህብረተሰቦች ርካሽና የቆሻሻ ፍጆታ ዕቃ መጣያ ሆነዋል ፤ በሌላ ወገን ደግሞ አብዛኛው ህዝብ ብዙ ቀናትና ወራት የለፋበትን የቡናም ሆነ የሰሊጥ ምርት በርካሽ ዋጋ እንዲሸጥ በመገደድ ወደ ባርነት እንዲለወጥ ተደርጓል። እንደዚህች ያለች አገራችንን በግሎባላይዜሽን መዳፍ ስር ወድቃ እንድትታሽ የምታደርግና ለህዝባችን የበለጠ ደሀ መሆን ተጠያቂ ከሆኑት አንዷ ፣ በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ድህረ-ገጽ አዘጋጆችና ግለሰቦች ስትወደስና የዐመቱ ምርጥ ሰው እስከመባል ካለማወቅ ዝናን አግኝታለች። ብዙዎቹ ሳያውቁት የድህነት ፍልፈላው አጋዥ ሆነዋል። አንድ ሰሞን ናዝሬት ድህረ-ገጽ ላይ አንድ ጽሁፍ አቅርባ ወደ አራት መቶ የሚሆን ደብዳቤ ተጽፎላታል። አባዛኛው የሚያሞግሳት ነበር። በዚህ መልክ ባለፈው ሃያ ዓመት በህብረተሰብአችን ውስጥ አዲስ ድህነትን ፈልፋይና የአገራችንን አቅጣጫና ዕድገቷን ያጣመመ እጅግ አደገኛ የህብረተሰብ ክፍል ብቅ ሊል ችሏል። ይህ የህብረተሰብ ክፍል በዓለም አቀፍ ደረጃ በተዋቀረው የፊናንስ መረብ ውስጥ በመካተት በካፒታሊስት አገሮች የሚካሄደውን የሀብት ክምችት(Capital Accumulation) አጋዥ ሆኗል። ወደ ውስጥ ደግሞ የህብረተሰቡን ሀብት በመምጠጥና የተንደላቀቀ ኑሮ በመኖር ለከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ምክንያት ሆኗል። በራሱ ዓለም ውስጥ የሚኖር ፣ ዐይን ያወጣና ህብረተሰቡም ወደ ጥፋት ሲያመራ ማየት

የማይችልና ፣ ማየት ቢችል እንኳ ደንታ የሌለው የህበረተሰብ ክፍል ነው። ፍልስፍና አልባ የሆነና ህብረተሰብአዊ ኖርሞችን መከተል የማይችል ፣ ወይም ህብረተሰቡ በተወሰነ ኖርሞች ላይ እንዲተዳደር ማድረግ የማይችል ከሰፊው ኢትዮጵያ ህዝብ ተነጥሎ የሚኖር ፣ የራሱ መዝናኛ ቦታና ልዩ የመገበያያ ቦታ(Shoping Center) ያለው ነው። በዚህ መልክ ብቻ ነው የዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም ብዙ የሶስተኛውን ዓለም አገሮች የሚቆጣጠረውና ለመቆጣጠር የሚችለው። በዚህም መልክ ነው የስልጣኔውን መንገድ የሚያሳስተውና ህብረተሰቦችን የሚያዘበራርቀው።

ዛሬ በአገራችን ምድር የሰፈነውን ፍልስፍና አልባ ፖለቲካና ህዝብን ማዋከብ ከዚህ ቀላል ሁኔታ በመነሳት ነው መመርመር መቻል ያለብን። በቀላል የሊበራል ዲሞክራሲና የነፃ ገበያ ፎርሙላ የህብረተሰብአችንን የተወሳሰበ ችግር ለመገንዘብ አንችልም። የአገዛዙ ችግር የፖለቲካ ፍልስፍና አልባነት ችግር ነው ስል ምን ማለቴ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ መታወቅ ያለበት ነገር አለ። ይኸውም ወያኔ/ኢህአዴግ ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ የፈለቀና የፊዩዳሊዝምና እጅግ የተዘበራረቀው ካፒታሊዝም ፣ አባዛኛዎቹ በአርባዎቹ መጨረሻና በሃምሳዎቹ መጀመሪያ ላይ ከአዋቂነትና ከብልህነት ፣ ከጥበብና ከቆንጆ ቆንጆ ስራዎች ይልቅ ፣ ተንኮለኛ ፣ ዳተኛና አራዳ እንዲሁም አገር ከፋፋይ አድርጎ ያወጣቸው ውጤቶች ናቸው። ከሰማይ የመጡ ወይም ከሌላ አገር ተሰድደው የመጡ አይደሉም። ምናልባት የዛሬዎቹ በአቶ መለስ የሚመሩት ግለሰቦች ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር ሲነፃፀሩ ልዩ የሚያደርጋቸው ፣ በተወለዱበት አካባቢ ካፒታሊዝም ከአዲስ አበባና ከአንዳንድ ክፍለ-ሀገሮች ጋር ሲወዳደር ሰርጎ ባለመግባቱ ትንሽም ቢሆን የኮስሞፖለቲካን ባህርይ ሊያድርባቸው አልቻለም። በአስተሳሰባቸው አንድ ወጥና ድርቅ ማለት ፣ በምንም ዐይነት ለሰው ልጅ አለማሰብ ፣ ወይም ህብረተሰብአዊ ፍቅር አለመኖር ፣ አሁንም ቢሆን ጦርነትንና ድንፋታን ማስቀደም ፣ ሶክራተስና ፓላቶ እንዳሉት ከህዝባዊ ስነ-ምግባርነት(Civic Virtu) ይልቅ ፣ ህብረተሰቡን ማመሰቃቀል ፣ ታዳጊው ትውልድ ኃላፊነት እንዳይኖረው ማድረግና ቀማኛ እንዲሆን ሁኔታውን ማመቻቸት ፣ ከፋፋይነትና ለውጭ ኃይሎች ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛትና ፣ ይህንን እንደትልቅ ፈሊጥ አድርጎ መያዝ ፣ ይህ ከሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ሲወዳደሩ ልዩ ሊያስመስላቸው ይችል ይሆናል ፤ ነውም። በተለይም ሀብትን ማካበትና ስልጣንን በሁሉም አቅጣጫ መቆጣጠር(Aquisition of Wealth and Power) ዐይነተኛ ባህርያቸው ሊሆን ችሏል። በዚህ አማካይነት ብቻ ስልጣናቸውን ለማጠናከርና ለረዥም ዐመታት ተደላድለው ሊገዙ የሚችሉ መስሏቸዋል። እስካሁንም ድረስ ተሳክቶላቸዋል። ከዚህም ስንነሳ ዕውናቸው በምንም ዐይነት የተስተካከለ ዕድገትን ማምጣትና ህብርተሰብአዊ እሴትን ማዳበር አይደለም። በአንዳንድ ነገሮች ከቀደመው የኃይለስላሴና የደርግ አገዛዝ ቢሮክራቶች የሚመመሳሰሉበት ሁኔታም አለ። ይኸውም ብሄራዊ ባህርይ ማጣት ፣ በተለይም ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሰጥ ለጥ ብሎ ማጎድብደድ ፣ ወይም አሜሪካንን እንደ አምላክ ማየትና አገርን መካድና የአገርን ምስጢር አሳልፎ መስጠት ፣ ሰፊውን ህዝብ መናቅና ተንኮሎኝነት ፣ በዚህ የሚመሳሰሉ ናቸው። ይህንን በጭንቅላታችን ውስጥ ስንቋጥር ነው የነገሮችን ሂደት መገንዘብ የምንችለው። ዝም ብሎ ግን አገዛዙ ለኢትዮጵያ አጀንዳ የለውም ፤ ማርክሲስት ነው ፤ የአልባንያውን ዐይነት ሶሻሊዝም ነው የሚያካሂደው ፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲን ነው የሚያራምደው ፤ ህገ-መንግስቱ ስታሊኒስታዊ ነው ፤ የሚሉት አነጋገሮች በዕውነቱ የህብረተሰብአችንን ስርዓትና የህሊና አወቃቀር እንዲሁም ደግሞ የታሪክን ሂደት ለመረዳት ካለመፈለግ ፣ ወይም ህብርተሰብአዊ አወቃቀሮች በሰው ልጅ አስተሳሰብ ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ባለማወቅ  የሚሰነዘሩ ፣ ታሪክን ሊያሰሩ የሚችሉ ከትንተና ዘዴዎች በመነሳት አይደለም የአገዛዙን ምንነት ለመረዳት ጥረት የሚደረገው። ዘጠና በመቶ የሚሆነው ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ተንታኝ ከራሱ ስሜት በመነሳት እንጂ አንዳች ፍልስፍናንና ስልትን (Methodology) በመከተል አይደለም የሚጽፈው። እንደዚህ ዐይነቱ ፍልስፍና አልባና ስልተ-ቢስ አቀራርብ ደግሞ የችግሩን ዋና ምንጭ እንዳንረዳ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ፣ ፍቱንና ህብረተሰብአችንን ሊያረጋጋና ወደስልጣኔ ሊያመራው የሚያስችል መፍትሄ እንዳንሰጥ ያደርገናል። ለመጻፍ ተብሎ የሚጻፍ ፣ ወይም ደግሞ የቁጭትን ለመወጣት ተብሎ የሚጻፍ ነገር የለም። በብዙዎች የሚቀርበው ሶፊስቲያዊ

የሚመስል አቀራረብና የፖለቲካ ስሌት በፍልስፍና ፣ በሳይኮሎጂና በህሊና ሳይንስ የሚደገፍ አይደለም። የአንድን ቡድን ወይም ግለሰብ ድርጊት ልንገነዘብ የምንችለው ከላይ የተቀመጡትን መሰረተ-ሃሳቦች ከቁጥር ውስጥ ያስገባን እንደሆን ብቻ ነው። ካለበለዚያ ስለፖለቲካና ህብረተሰብን ስለመግንባት ሳይሆን ተረት ተረት ነው የምናወራው ማለት ነው። ተረትም ቢሆን እንኳ ራሱ ልክ እንደምትዮሎጂ በአንድ የታሪክ ወቅት የሚገኝን ህብረተሰብ ሁኔታና አስተሳሰቡን ነው የሚገልጽልን።

ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አወቃቀር ፣ ብሄራዊ ባህርይ ኃይል አለመኖር ፣ ሰፋ ያለ ምሁራዊ ኃይል ብቅ ማለት ያለመቻሉ ፣ በተለይም በአብዮቱ ወቅት የተማረው ኃይል እንዳለ ሙጥጥ ብሎ ማለቁ ፣ የቀረው ደግሞ ነገረ-ዓለሙን እርግፍ አድርጎ መቀመጡ ፣ ወይም ደግሞ በድሮው አቋሙ ገፍቶ መሄድ አለመቻሉ ፣ እነዚህ ሁሉ ተደምረው ለወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ የፖለቲካ ስልጣንን እንዲጨብጥ ሁኔታውን አመቻችተውለታል። ማንም የሚቋቋመው ሲያጣ ፍቅርና ሰላምን ከማስቀደም ይልቅ እንደልቤ መፈንጫ አገኘሁ በማለት ህብረተሰቡን ማዋከብ የፖለቲካው ዘዬ አድርጎ ተያያዘው። የህበረተሰቡን ሀብት በመንጠቅና ጥቂቶችንም በማባለግ እያበጠ መምጣት ጀመረ። ከኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ዕርዳታ ሲፈስለት እኔነኝ ብቸኛው ኃይል በማለት በግሎባላይዜሽን ጉያ ስር በመውደቅና በመታሸት የህብረተሰቡን ችግር ውስብስብ አደረገ። የአቶ መለስ አገዛዝ በ20 ዐመታት የአገዛዝ ዘመኑ ልክ ሶክራተስ ፐሪክለስን እንደወነጀለው ፣ ሰነፍ ፣ ለፍላፊ ፣ አጭበርባሪ ፣ አገር ሻጭና ከሃዲ ፣ በዝሙት ዓለም ውስጥ የሚዋኝ ፣ ዕውነትን ከመፈለግ ይልቅ ለውሸት ጠበቃ የቆመ ትውልድ ፣ በግልጽ የሚታዩ ነገሮችን የሚክድና ፣ ተቀባይ ሲያጣ ደግሞ ጠበንጃ የሚሰነዝር ትውልድ አፍርቷል። ይሁንና ግን አቶ መለስ ከነ ፐሪክለስ ጋር ሊወዳደሩ የሚችሉ መሪ አይደሉም። ፐሪክለስ በሌሎች የግሪክ ግዛቶች ላይ የአቴንን የበላይነት ለማስፈን የታገለና በአቴን ስልጣኔ የሚኮራ ነበር። የአቶ መለስ አገዛዝ ግን „ከአሜሪካን ጋር እየተመካከርን ነው የምንሰራው" በማለት የበታችነቱን የሚያረጋግጥና ፣ ለስልጣኔ ጠንቅ የሆነ አገዛዝ ነው። የዓለም የገንዘብ ድርጅትንና የዓለም ባንክን የኒዎ-ሊበራል አንጀት አጥብቅ የሞኔትሪስቲክ ፖሊሲ በመከተልና በዚህ በመዝናናት ድህነትን የሚፈለፍል ነው። የዚህ ሁሉ ምንጭ በስልጣን መታወርና ማንአለብኝ ብሎ እየተመጻደቁ መኖር ነው። ለዚህ ሁሉ መመፃደቅና የወያኔ ማንአለኝበት ደግሞ የፖለቲካ ተቃዋሚ ነኝ የሚለውና ህብረተሰቡን የሚያዘናጋው ኃይል የራሱ አስተዋጽኦ አለው። ተቃዋሚ ነኝ የሚለው ኃይል አገራችን በእርግጥስ ወዴት እንደምታመራ በደንብ የገባውና ፣ እዚያው አገር ውስጥ እያለ በአገር ቤት ውስጥ የሚካሄደውን ትርምስ በደንብ የሚከታተል የሚመስል አይደለም። አንዳንዴ መግለጫ ከመስጠትና ለውጭ ኃይሎች የይድረሱልኝ ጩኸት ከማሰማት በስተቀር በከፍተኛ ምሁራዊ ንቃተ-ህሊና አገዛዙን ሊጋፈጥ የሚችል አይደለም። በዚህ ዐይነት በውሸት ላይ በተመሰረተ አገዛዝና እጅግ በደከመ ህብረተሰብአዊ እንቅስቃሴ ምክንያት የተነሳ ህዝባችን ሞራሉ እንዲዳሽቅ ሆኗል። ዕውነተኛ ፍቅር ከልቡ ተደምስሶ ጠፍቷል። ደስታ ምን እንደሆን እንዳያውቅ ተደርጓል። በሀዘን ዓለም ውስጥ እንዲኖር ተፈርዶበታል። ግራ የገባው ፣ ለምን እንደሚኖርና ወዴት እንደሚጓዝ የሚያውቅ አይደለም። ለማኝ እንዲሆን ተደርጓል። በራሱ ላይ ዕምነት እንዲያጣ ሆኗል። ተፈጥሮአዊ ነፃነቱን ተገፏል። ወጣት ልጆቹን ለውጭ ከበርቴዎች ካለ ዕድሜያቸው ለጋሽ እንዲሆን ተደርጓል። ብሄራዊ ነፃነታችን ተገፏል። በአንድ በኩል አስረሽ ምችው ፣ በሌላው ወገን ደግሞ ተስፋ መቁረጥና መዘናጋት የህብረተሰብአችን ልዩ ባህርይ ሆነዋል።

ከዚህ የተወሳሰበና አገርን ለማውደም ከተቃረበ ችግር እንዴት እንወጣለን? የሚለው ነው ዋናው ጥያቄያችንና መመለስ ያለብን ተግባር። በተራ የነፃ ገበያና የሊበራል ዲሞክራሲ ፎርሙላ ፣ ወይስ አስቸጋሪ በሆነው ግን ደግሞ ፍቱን በሆነው በሬናሳንስ ፍልስፍና አማካይነት ነው የተወሳሰበውን የህብረተሰብአችንን ችግር ልንፈታ የምንችለው? በእኔ ዕምነት ተራ የሊበራል ዲሞክራሲና የነፃ ገበያ ፎርሙላዎች ለኛ ብቻ ሳይሆኑ ለሌሎች የአፍሪካ አገሮችም ችግር በፍጹም መፍትሄ ሊሆኑ አይችልም። መፍትሄው የመንፈስን የበላይነት የሚያስቀድመውን የሬናሳንስን ዐይነት የሁሉ-ገብ የህበረተሰብን ችግር መፍቻ ስልት የተከተለን እንደሆን ብቻ ነው። እኛ ብቻ ሳንሆን ዛሬ የተቀረው የዓለምም ህዝብ

የሚመኘው የመንፈስን የበላይነት የሚያስቀድምና የኑሮን ትርጉም እንድንረዳ የሚያደርገንን መንገድ ነው። ከየት እንደመጣን ፣ በዚህ ዓለም ላይ ለምን እንደምንኖርና ፣ ምንስ ማድረግ እንዳለብንና ወዴትስ እንደምናመራ እንድንገነዘብ የሚያደርገን። ለዚህ ሁሉ መፍትሄውም የፒታጎራስን ፣ የሶክራተስንና የፕላቶንን ወንድማዊ ወይም የእህትማማች ፍቅር እንደመመሪያ አድርገን የወሰድን እንደሆን ብቻ ነው። ይህ ፍቅር ግን በዕውቀት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። ምሁራዊ ፍቅር ማለት ነው። ዕውነትን ለመፈለግ የሚረዳንና ሶፊስታዊዉን የመሙለጭለጭ መንገድ አሸቀንጥረን የሚያስጥለን መሆን አለበት። በሃሳብ እንድንገናኝ የሚያደርገንና ፣ ራሳችንን አውቀንና ለውጠን ህብረተሰብአችንን ከገባበት ማጥ ውስጥ እንዲወጣ የሚያስችለው ፍልስፍናና መመሪያ መሆን አለበት።

**ፈቃዱ በቀለ**

fekadubekele@gmx.de